# በአሜርካ ኤርትራዊ ጋዜጠኛውን የደበደቡ የኢሳያስ ደጋፊዎች ተፈረደባቸው

*በካሳሁን ለማ*



ሂውስተን፣ ቴክሳስ - የፕሬዘዳንት ኢሣያስ አፈወርቂ መንግስት ደጋፊ የሆኑ ሁለት ኤርትራዊያን በስደት የሚገኝ ጋዜጠኛ ቴዎድሮስ መንግስቱ በመደብደብ ወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው ተፈረደባቸው። ቅጣታቸውም በአስቸኳይ ተግባራዊ እንዲሆን መመሪያ ተላልፏል።

በአሜሪካ የኤርትራ ኢምባሲ ተወካይና በስደት የሚኖሩ ኤርትራዊያን ማህበረሰብ አስተባባሪ ኮሚቴ ጋር ቀጥተኛ ግኑኝነት እንዳላቸው የሚነገርላቸው ረዲ በኩረ ፅዮን እና ዮሐንሥ ገብረ ሚካኤል የተባሉ ግለሰቦች ይህን የድብደባ ወንጀል የፈፀሙት ባለፈው ሜይ 9, 2010 በቴክሳስ ሂውስተን በተጠራው የኤርትራ መንግስት ድጋፍ ሰጪ ስብሰባ በተነሳው አምባጓሮ መሆኑ ታውቋል።

ከላይ በተጠቀሰው ቀን ግጭቱ ሊነሳ የቻለው ጋዜጠኛ በስብሰባው ለመገኘት በቦታዉ እንደደረሰ የስብሰባው አዘጋጆች ጥሪው እሱን እንደማይመለከትና ለኤርትራ መንግሥት ደጋፊዎች ብቻ መሆኑን በመግለጻቸው ነበር ። የስብሰባው ዋና ዓላማ በወቅቱ አሜሪካ ኤርትራ አል ሻባብን ትረዳለች በሚል ምክንያት ላይ የጣለችውን የጦር መሣሪያ ሽያጭ ዕቀባና እርዳታ ለማውገዝ የተጠራ ነበር። ይሁንእንጂ ጋዜጠኛ ቴድሮስ ስብሰባው የኤርትራዊያን እስከሆነ ድረስ እንደሚመለከተው፣ ስብሰባውን ራሱ በሚያሳትመው ጋዜጣ ዜና ሊሰራበት እንደሚፈልግ ያስረዳቸዋል። ሆኖም የስብሰባው አስተባባሪዎች እንደቴዎድሮስ ዓይነት የኢሣያስ መንግስት ተቃዋሚ ጋዜጠኛ ወደ ስብሰባው መግባት እንደማይፈቀድ አበክረው ለማሳመን ይሞክራሉ።

(ዜናውን በእንግሊዝኛ ያንቡ - http://cpj.org/blog/2010/06/for-eritrean-expatriate-press-intimidation-in-exil.php )

ሁኔታው ወደ አለመግባባት አቅጣጫ ያመራል። በመካከሉ ከዋሽንግተን ዲሲ ስብሰባውን ለመምራት በቦታው የተገኙ የኤርትራ ኢምባሲ ባለስልጣናትና ጥቂት ተሰብሳቢዎች ቴዎድሮስ መንግስቱ አስመራ የነበረና የኢሳያስ አፈወርቂ መንግሥት ዋንኛ ተቃዋሚ ጋዜጠኛ መሆኑን ይገነዘባሉ። ይሄኔ ከግራና ከቀኝ የድብደባ ጥቃት ይፈራረቅበታል ። ገላጋይ ለጊዜው ያልተገኘለት ይኸው ድብደባ በጋዜጠኛው የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ላይ ጉዳት አስከትሏል። ፊቱም ያብጣል። በቦታው ዘግይቶ የደረሰው የሂውስተን ከተማ ፖሊስ ተጎጂውን ሆስፒታል ከላከ በኋላ ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ሥር አውሎ ምርመራ መጀመሩ ለመገንዘብ ተችሏል።

የሂውስተን ከተማ ፖሊስ ላለፉት ወራት ተጠርጣሪዎችን ፈፅመዋል የተባለውን ወንጀል ሲመረምር ቆይቷል። በዚህም ዓይነት ከጉዳዩ ጋር ግኑኝነት አላቸው የተባሉ የሰውና የቴክኒክ ማስረጃ ሲያሰባስብ እንደቆየ ለመረዳት ተችሏል። ተጠርጣሪዎች ጉዳዩ እልባት እስኪያገኝ ድረስ ከአካባቢው እንዳይርቁ ማስጠንቀቂያ ተሠጥቷቸው እንደነበርና፣ ፓስፖርታቸውንም እንዲያስረክቡ መደረጋቸው ተመልክቷል። በዚህም መሠረት ተጠቃሽ ግለሰቦች በፈጸሙት የድብደባ ወንጀል የሂውስተን ከተማ ፍርድ ቤት ጥር 11 ቀን 2012 በዋለው ችሎት ሁለቱም ላይ የጥፋተኝነት ብይን ሰጥቷል። በማግሥቱ ለፍርድ የተቀመጠው ይኸው የዳኝነት አካል ሁለቱም የዘጠኝ ወር የነፃ ኮሚኒቲ አገልግሎት እንዲሠጡ ወስኗል፣ ከዚህም ጎን ለጎን በኮሚኒቲ አገልግሎት ላይ እያሉ ጋዜጠኛውን የመተናኮል አዝማሚያ ካሳዩ የአንድ አመት እሥራት እንደሚጠብቃቸው በውሳኔው መዝገብ ውስጥ ተጠቅሷል።

ጋዜጠኛ ቴዎድሮስ መንግስቱ ከተማ በአሥመራ በተለያዩ ሚዲያዎች በጋዜጠኝነት ሞያ ሲያገለግል እንደነበር ፣ በኋላም የፕሬዘዳንት ኢሣያስ አፈወርቂ መንግሥት የሚያደርስበትን እስራትና እንግልት አማሮት ከሀገሩ እንደተሰደደ ስለ እሱ የተፃፉ ዘገባዎች ያስረዳሉ። አሜሪካም ከመጣ በኋላ በሂውስተን ነዋሪ ለሆኑ ኤርትራዊያን አንባቢዎች "ሰላም" የተባለች ጋዜጣ በትግሪኛ ቋንቋ በየወሩ እያሳተመ በማሠራጨት ይገኛል።

(ሪፖርቱን ያንቡ - http://awate.com/texas-jury-two-pro-government-eritreans-guilty-of-assaulting-eritrean-journalist/ )
ኤርትራ እንደ ኢትዮጵያ ከመሣሠሉ የፕሬስ ነፃነት ፈፅሞ ከጨለመባቸው አገሮች የመጨረሻዎቹ ተርታ ጎን የተመደበች መሆኗ ይታወቃል። ይህ ዓይነቱ ክስተት ከዚህ ቀደም በአሜሪካ መሬት ያልተፈጸመ መሆኑን ደግሞ ማስረጃዎች ያስረዳሉ።